ቁጥር፡- ሕ/ም/ማ/ማ/ዳ/1488/18

ቀን፡- 29/12/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ገቢዎች ቢሮ

ባህር ዳር

ጉዳዮ፡ **የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል**

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ. ም. እና በዚህ አዋጅ ማሻሻያ መሠረት ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አስመልክቶ አዋጁ በወጣ በ2 (ሁለት) ዓመት ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮ በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል።

በዚህም መሠረት ቢሯችሁ በቁጥር ገቢዎችም.ቢ/3.8/265፣ በቀን 27/11/2018 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ሽኝ ደብዳቤ "የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር አገቢ29/2017 ዓ.ም." ተብሎ የተገለጸ እንድንመዘገብላችሁ የላካችሁልን መሆኑ የሚታወቅ ነው።

በእኛም በኩል የተላከልንን ይህን መመሪያ በአዋጁ መሠረት ከተመለከትን በኃላ፣ በክልል ደረጃ "የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር መመሪያ ቁጥር 176/2018 ዓ.ም." በሚል መዝግበነዋል።

በመሆኑም መመሪያውን በተመዘገበው ቁጥር መሠረት ሥራ ላይ እንድታውሉ እየገለጽን፣ የመዘገብነውን መመሪያ 13 ገጽ በዚህ ሽኝ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክንላችሁ መሆኑን እናሳውቃለን።

ከሰላምታ ጋር

መስፍን መኮነን

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤(ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክት/ል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

ፍትህ ቢሮ

መመሪያ ቁጥር 176/2018 ዓ.ም.

የአማራ ክልል ገቢዎች ቢሮ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ

በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ በወቅቱ ወይም በአንድ ጊዜ መክፈል ለማይችል ታክስ ከፋይ ገቢዎች ቢሮ ክፍያ ጊዜ ለማራዘም እንደሚችል የተደነገገ በመሆኑ፣

ገቢዎች ቢሮ ታክስ ከፋዮች የክፍያ ግዴታቸውን እንዲወጡ ተገቢነት ያላቸውን ሁኔታዎች በማመቻቸት ድጋፍና እገዛ ማድረግ የሚጠበቅበት በመሆኑ፣

ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ በአንድ ጊዜ መክፈል በማይችልበት ጊዜ የተራዘመ የእዳ መክፈያ ጊዜ ስምምነት በማስገባትና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚስተናገድበትን ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ስለሆነ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 61(2) እና 135(3) በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር 176/2018 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

1/ " የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ" ማለት ማንኛውም ታክስ ከፋይ በአዋጁ መሠረት የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ወይም በወቅቱ ያልተከፈለ የታክስ እዳን ለመክፈል ጊዜ እንዲራዘምለት ሲያመለክት ከመደበኛው የታክስ መክፈያ ጊዜ በተለየ ሁኔታ እንዲከፍል የሚሰጥ የክፍያ ጊዜ ነው።

2/ "የክፍያ ጊዜ ስምምነት" ማለት ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ ማለትም ታክስ፣ ወለድ እና ቅጣት በአንድ ጊዜ መክፈል ሳይችል ሲቀር ታክስ ከፋዩ እና ገቢዎች ቢሮ ክፍያው የሚፈጸምበትን ጊዜ እና ሁኔታ በተመለከተ በጽሁፍ የሚያደርጉት የስምምነት ውል ነው።

3/ "የታክስ ከፋዮች ምደባ" ማለት ገቢዎች ቢሮ በሚያወጣው መስፈርት መሰረት የደረጃ "ሀ"፣ የደረጃ "ለ" እና የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የሚስተናገዱበት መምሪያ ወይም ጽ/ቤት ነው።

4/ "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት በተወሰነ አካባቢ በግብር ከፋዮች በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ማለትም በተፈጠረ ጦርነት፣ በንግድ ስራ ላይ ጫና የሚፈጥር ጦርነት፣ ጎርፍ፣ ቃጠሎ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መብረቅ፣ ተምች ወይም ሌላ ተመሳሳይ ክስተት ሲያጋጥም ነው።

5/ "ሃብቱ በዕዳ የተያዘበት" ማለት የታክስ ዕዳ ያለበት ታክስ ከፋይ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ለታክስ ዕዳ ማካካሻነት የገቢዎች ቢሮ የተረከበው ማለት ነው።

6/ "የታክስ ህግ"ማለት የገቢ ግብር አዋጅ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፣ የቴምብር ቀረጥ አዋጅና የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ነው።

7/ "የታክስ ዕዳ" ማለት እንደ አግባቡ በታክስ ህጎች መሠረት በመክፈያ ጊዜው መክፈል ሲገባው ያልተከፈለ ታክስ እና ወለድ እንዲሁም አስተዳደራዊ መቀጫዎችን ይጨምራል።

8/ "ዋስትና" ማለት የታክስ ክፍያ ጊዜ እንዲራዘምለት የጠየቀ ታክስ ከፋይ በገቢዎች ቢሮ ሲጠየቅ የሚያቀርበው የባንክ ወይም የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀስ ንብረት ዋስትና ነው።

9/ "የማይነሳ አስተዳደራዊ ቅጣት" ማለት በአስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ መሠረት እንዲነሳ ያልተፈቀደው እና የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነቱ አካል የሆነው ተከፋይ አስተዳደራዊ ቅጣት ነው።

10/ "ያልተከፈለ ታክስ" ማለት በመክፈያ ቀን ወይም ገቢዎች ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 32 የተመለከተውን የታክስ መክፈያ ጊዜ ያራዘመ ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ ቀሪ ታክስ ማለት ነው።

11/ "የታክስ ጊዜ" ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት የታክስ ማስታወቂያ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብ ነው።

12/ "የታክስ ስሌት " ማለት የራስ ታክስ ስሌት፣ በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት፣ የስጋት ታክስ ስሌት፣ የተሻሻለ ታክስ ስሌት፣ አስተዳደራዊ ቅጣት፣ ወለድ ወይም በታክስ ህግ መሠረት የሚደረግ ማንኛውም ስሌት ነው።

13/ "የራስ ታክስ ስሌት" ማለት በገቢዎች ቢሮ ባጸደቀው ቅጽ መሠረት ታክሱን የማስላት ግዴታ ባለበት ታክስ ከፋይ የተዘጋጀ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ማለት ነው።

14/ "አዋጅ " ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ነው።

15/ "ገቢዎች ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ ማለት ሲሆን በየደረጃው የሚገኙ የገቢ ተቋማትንም ይጨምራል።

16/ "ኃላፊ" ማለት የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይም የሚወክለው የሥራ ኃላፊ ወይም በየደረጃው የሚገኝ የገቢዎች መምሪያ ወይም ጽ/ቤት ኃላፊ ነው።

17/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ፣ደንብ እንዲሁም የታክስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1/ በወቅቱ መክፈል ያለበትን ታክስ ወይም የመክፈያ ጊዜው ያለፈበትን ያልተከፈለ ታክስ በአንድ ጊዜ መክፈል በማይችልና የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ በሚጠይቅ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት ስለሚፈቀድባቸው ወይም ስለሚከለክልባቸው ሁኔታዎች

4. የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች

በዚህ መመሪያ መሰረት የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የሚፈቀደው፦

1/ ታክስ ከፋዩ የታክስ እዳውን በአንድ ጊዜ መክፈል የማይችል ሲሆን ነው።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በከፍተኛ ሃብቱ እንዲያዝ የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበት ወይም ንብረቱ እንዲሸጥ ጨረታ የወጣበት ታክስ ከፋይ ዕዳውን ለመክፈል ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ለዕዳው ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ወይም የንብረት ዋስትና ሲያቀርብ የክፍያ ማራዘሚያ የሚፈቅድ ይሆናል።

5. የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች

1/ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) በታክስ ማስታወቂያ (በራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ) ማቅረቢያ ጊዜ መክፈል ያለበት የታክስ እዳ ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ ወይም ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ መደረግ ያለበት ግብር ሲሆን፣

ለ) ታክስ ከፋዩ አስቀድሞ የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተሰጠው ሆኖ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ

ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሳይኖር እዳውን ያልከፈለ ሆኖ ሲገኝ፣

ሐ) የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተጠየቀበት የታክስ እዳ መጠን እንደ ታክስ ከፋዩ አመዳደብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 3 ከተቀመጠው አነስተኛ የገንዘብ መጠን በታች ከሆነ፣

2/ ታክሰ ከፋዩ :-

ሀ) ለዕዳው ማስከፈያ ሀብቱ እንዲያዝ የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበት ከሆነ፣

ለ) በእዳው የተያዘበትን ንብረት ለመሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ የወጣበት ከሆነ፣

6. ለታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ማመልከቻ መልስ ስለመስጠት

ለዚህ መመሪያ መሠረት በቀረበ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ማመልከቻ ላይ የገቢዎች ቢሮው የሰጠውን ውሳኔ የሚገልጽ የጽሁፍ ማስታወቂያ ማመልከቻው በቀረበ በ14 ቀናት ውስጥ ለታክስ ከፋዩ መሰጠት አለበት።

ክፍል ሦስት

የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት ስለሚፈቅደው አካል፣ የመክፈያ ጊዜና አከፋፋሉ

7. የክፍያ ጊዜ ስምምነትን ስለሚፈቅደው አካል እና የጊዜ ገደብ ስለመወሰን

1/ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8 የተደነገገው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከዝቅተኛው የታክስ ዕዳ መጠን በታች ሆኖ ታክስ ከፋዩ በአንድ ጊዜ መክፈል የማይችል መሆኑ ከተረጋገጠ የከተማ ወይም የወረዳ ወይም የክፍለ ከተማ ገቢ ጽ/ቤት ኃላፊ ከ3 ወር ላልበለጠ ጊዜ እንዲራዘምለት ሊፈቅድ ይችላል።

2/ ታክስ ከፋዩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ የሚከፍለውን የንግድ ትርፍ እና ኪራይ ግብር መክፈል አለመቻሉን ጠቅሶ ሲያመለክት ጥያቄውን የከተማ ወይም የወረዳ ወይም የክፍለ ከተማ ገቢ ጽ/ቤት ኃላፊ አሳማኝ ምክንያት መሆኑን ሲያረጋግጥ ከ3 ወር ላልበለጠ ጊዜ እንዲራዘምለት ሊፈቅድ ይችላል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ለ 3 ተከታታይ የግብር ዘመን ተመሳሳይ ጥያቄ የሚያቀርብ ከሆነ የታክስ ማራዘሚያ ጊዜ ሊፈቀድለት አይችልም፣

4/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የ3 ወር ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በታክስ ከፋዩ ማመልከቻ ቀርቦ የከተማ ወይም የወረዳ ወይም የክፍለ ከተማ ገቢ ጽ/ቤት ኃላፊ ቀርቦ ውሳኔ ካገኘበት ቀን ቀጥሎ ባለው ቀን ጀምሮ ይሆናል።

8. <u>የታክስ እዳ የመክፈያ ጊዜ ስለመወሰን</u>

ታክስ ከፋዩ የታክስ ስሌት ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሶት በዚህ መመሪያ መሠረት የታክስ ክፍያ ማራዘሚያ ጊዜ ስምምነት ውል ሲገባ የዕዳው የመክፈያ ጊዜ የሚወሰነው በሚከተለው አግባብ ይሆናል።

1/ <u>የደረጃ "ሀ"</u> ታክስ ከፋዮች በሚስተናገዱበት የገቢዎች ጽ/ቤት የታክስ ስሌት ውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ፍሬ ታክስ፣ መቀጫ እና ወለድ ዕዳ፡-

ሀ) ከብር <u>200,000</u> /ሁለት መቶ አንድ ሺህ / እስከ <u>500,000</u> /አምስት መቶ ሺህ/ ከሆነ እስከ <u>3 ወር</u>፣

ለ) ከብር <u>500,001</u> /አምስት መቶ ሺህ አንድ/ እስከ <u>1,500,000</u>/ አንድ ሚሊየን አምስት መቶ ሺህ / <u>6 ወር</u>፣

ሐ) ከብር <u>1,500,001</u>/ አንድ ሚሊየን አምስት መቶ ሺህ አንድ /እስከ ብር <u>3,000,000</u>/ ሦስት ሚሊየን / እስከ <u>8 ወር</u>፣

መ) ከብር <u>3,000,001</u>/ ሦስት ሚሊየን እንድ ሽህ / እስከ <u>5,000,000</u>/ አምስት ሚሊየን <u>10 ወር</u>፣

ሠ) ከብር <u>5,000,00</u>/ አምስት ሚሊየን / በላይ ከሆነ <u>12 ወር</u> የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

2/ <u>የደረጃ "ለ"</u> ታክስ ከፋዮች በሚስተናገዱበት የገቢዎች ጽ/ቤት የታክስ ስሌት ውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ፍሬ ታክስ፣ መቀጫ እና ወለድ ዕዳ፡-

ሀ) ከብር 50,000/ ሃምሳ ሽህ/ እስከ 125,000 / አንድ መቶ ሃያ አምስት ሽህ / ከሆነ እስከ 3 ወር፤

ለ) ከብር 125,001 /አንድ መቶ ሃያ አምስት ሽህ አንድ / እስከ ብር 750,000 /ሰባት መቶ ሃምሳ ሽህ/ /ከሆነ እስከ 6 ወር፤

ሐ) ከብር 750,001 /ሰባት መቶ ሃምሳ ሽህ አንድ/ እስከ ብር 2,500,000 /ሁለት ሚሊያን አምስት መቶ ሽህ /ከሆነ እስከ 8 ወር፤

መ) ከብር 2,500,001 /ሁለት ሚሊያን አምስት መቶ ሽህ አንድ/ እስከ 3,750,000 / ሶስት ሚሊየን ሰባት መቶ ሃምሳ ሽህ / ከሆነ እስከ 10 ወር፤

ሠ) ከብር እስከ 3,750,000 / ሶስት ሚሊየን ሰባት መቶ ሃምሳ ሽህ አንድ / በላይ ከሆነ እስከ 12 ወር የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

3/ የደረጃ "ሐ" ታክስ ከፋዮች በሚስተናገዱበት የገቢዎች ጽ/ቤት የታክስ ዉሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ፍሬ ታክስ፣ መቀጫ እና ወለድ ዕዳ፡-

ሀ) ከብር 2,500/ሁለት ሺህ አምስት መቶ/ እስከ ብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ/ ከሆነ እስከ 3 ወር፤

ለ) ከብር 25,001 /ሃያ አምስት ሺህ አንድ/ እስከ ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ /ከሆነ እስከ 6 ወር፤

ሐ) ከብር 50,001 /ሃምሳ ሺህ አንድ ብር / እስከ ብር 75,000/ ሰባ አምስት ሽህ /ከሆነ እስከ 8 ወር፤

መ) ከብር 75,001 /ሰባ አምስት ሽህ ሁለት አንድ ብር / እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ብር ብቻ) ከሆነ እስከ 10 ወር፤

ሠ) ከብር 100,001 (አንድ መቶ አንድ ሽህ) በላይ ከሆነ እስከ 12 ወር፤ የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

4/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በግብር ከፋዮች ደረጃ የተቀመጡ ሁኔታዎች መሟላታቸው ተረጋግጦ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተሰጠው ታክስ ከፋይ ከገቢዎች ቢሮ ጋር የክፍያ ጊዜ ስምምነት እንዲፈርም ይደረጋል።

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ማዕቀፍ፣ ማርቀቅና ሕጋዊነት ዳይሬክቶሬት

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሠረት የታክስ ዕዳ ፍሬ ታክስ፣ ወለድ፣ መቀጫ ያካተተ ከሆነ በአስተዳደራዊ መቀጫ አነሳስ መመሪያ መሠረት የማይነሳው መቀጫ መጠን ብቻ ተሰልቶ የውሉ አካል የሚደረግ ሲሆን መቀጫው የሚነሳው በውሉ ውስጥ የተካተተው ፍሬ ታክስ ፣ ወለድና የማይነሳ መቀጫ እንዲከፈል ከተደረገ በኋላ ይሆናል፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት ታክስ ከፋዩ የመጀመሪያ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል ተፈራርሞ ግዴታውን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መወጣት ያልቻለ ሆኖ በድጋሜ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ እንዲሰጠው ከማስረጃ ጋር ጥያቄውን ሲያቀርብ የታክስ እዳ ክትትል ባለሙያ ወይም የግብር አወሳሰን፣ አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት አስተባባሪ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለመምሪያ ወይም ለጽ/ቤት ኃላፊ በማቅረብ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የቀረበለት የሥራ ኃላፊ ማስረጃውን በመመዘን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 በተደነገገው የመክፈያ ጊዜ አሰጣጥ ሥርዓት መሠረት እዳውን እንዲከፍል በድጋሚ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 እና 7 የተደነገገው ቢኖርም በድጋሜ የክፍያ ስምምነት ውል ተፈራርሞ ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ ሌላ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት ሊፈቀድለት አይችልም፡፡

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት በድጋሜ የክፍያ ማራዘሚያ ስምምነት የተሰጠው ታክስ ከፋይ ድጋሜ ስምምነት ከሚገባበት የታክስ ዕዳ ላይ ቅድሚያ 25% መክፈል ይኖርበታል፡፡

ክፍል አራት

የታክስ ዕዳ ክፍያ ማራዘሚያ ጥያቄ አቀራረብ ፣መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና የአፈጻጸም ሥርዓት

9. የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ እንዲፈቀድለት የሚጠይቅ ታክስ ከፋይ ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት በሚገባባቸው የታክስ ዕዳዎች ቢያንስ 25% /ሃያ አምስት በመቶ/ ቅድሚያ ክፍያ መከፈል አለበት፡፡

2/ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ የቀረበው የታክስ ከፋዩ ሀብት ለዕዳው ማስከፈያ ከተያዘ በኋላ ከሆነ የገቢዎች ቢሮ ጉዳዩን ለማስፈጸም ያወጣቸውን ወጪዎች እና ቢያንስ የታክስ ዕዳውን 25% /ሃያ አምስት በመቶ/ ቅድሚያ ክፍያ መከፈል አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከተውን ለማስፈፀም ለታክስ ዕዳ ሀብት የተያዘበት ታክስ ከፋይ ዕገዳው ሊነሳለት የሚችለው ለዕዳው ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ዋስትና ወይም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ቋሚ ሀብት ከሚመለከተው አካል አስገምቶ እና እንዳይሸጥና እንዳይለወጥ አሳግዶ ዋስትና ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሱት ቅድሚያ ክፍያ ለመወሰን የስሌት መሠረቱ ዋና ታክስ፣ ወለድና የማይነሳው መቀጫ መጠን ይሆናል፡፡

5/ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ወይም በፍርድ አፈፃፀም ላይ የሚገኝ ከሆነ ታክስ ከፋዩ ገቢዎች ቢሮ የታክስ ዕዳ አሰባሰቡን ለመከታተል ያወጣቸውን ወጪዎች በሙሉ እንደ አግባብነቱ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ወይም /2/ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ጋር በቅድሚያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

6/ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሶት በውሳኔው ላይ ባለመስማማት ለደንበኞች አገልግሎት ዋና የስራ ሂደት ቅሬታውን ሲያቀርብ አምኖ የከፈለውን ታክስ ወይም ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅሬታውን ሲያቀርብ የከፈለውን ታክስ የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት በሚገባበት ጊዜ ለቅድሚያ ክፍያው እና ለቀሪ ዕዳው ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ወይም /2/ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን እና በመክፈያ ጊዜ የሚፈጸመው የአከፋፈሉ ቅደም ተከተል በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 34 መሰረት ይሆናል፡፡

8/ ቅድሚያ ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ላሉት ቀሪ ክፍያዎች የመክፈያ ጊዜው የሚታሰበው ቅድሚያ ክፍያው ከተፈጸመበት በየ 30ኛው ቀን ላይ ይሆናል፡፡

9/ በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተገባበት የታክስ ክፍያ በታክስ ሕጉ መሠረት መክፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ እስከተከፈለበት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው ስሌት መሠረት ወለድ ይከፈልበታል፡፡

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 የተመለከተውን ለማስፈጸም በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ ጠቅላላ መጠን በታክስ ክፍያ ካልተከፈለው ዋና ታክስ ሊበልጥ አይችልም፡፡

11/ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ ወይም ታክሱን የክፍያ ጊዜ ስምምነት ገብቶ በመክፈል ላይ ያለ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 104 መሰረት ታክስን አዘግይቶ መክፈል የሚያስከትለው ቅጣት አይታሰብበትም፡፡

12/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /12/ ድንጋጌ ቢኖርም ታክስ ከፋዩ በገባው የክፍያ ጊዜ ስምምነት መሠረት መክፈል ያለበትን የታክስ ዕዳ ሳይከፍል ያቋረጠ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

10. <u>የኤሌክትሮኒክስ ዘዴን ስለመጠቀም፤</u>

1/ ታክስ ከፋዩ የታክስ ክፍያ ማራዘሚያ ለመጠየቅ የሚቀርብን ማመልከቻ የኤሌክትሮኒክስ ዘዴን በመጠቀም ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2/ የገቢዎች ቢሮ በቀረበለት የክፍያ ማራዘሚያ ጥያቄ ላይ ምላሽ ለመስጠትና ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ከታክስ ከፋዩ ጋር የሚያደርጋቸው ሌሎች ግንኙነቶች የኤሌክትሮኒክስ ዘዴን በመጠቀም ሊያከናውን ይችላል፡፡

11. <u>በልዩ ሁኔታ የሚሰጥ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ</u>

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4፣ 5፣ 7፣ 8 እና 9 ላይ የተመለከተው ቢኖርም የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይም የሚወክለው የስራ ኃላፊ በልዩ ሁኔታ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመላከተው ቢኖርም በልዩ ሁኔታ የሚሰጥ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ከ 2 ዓመት በላይ አይበልጥም፡፡

3/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው የክፍያ ማራዘሚያ ጊዜ 2 ዓመት የሚሰጠው ከዚህ በፊት ያልተሰጠው ከሆነ ነው።

4/ በልዩ ሁኔታ የመክፈያ ጊዜ እንዲራዘም የሚቀርቡ ጥያቄዎች የሚያቀርቡት ለክልሉ ገቢዎች ሆኖ የመምሪያውን ወይም የጽ/ቤቱን የውሳኔ ሃሳብ አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል።

5/ መምሪያው ወይም ጽ/ቤቱ ከታክስ ከፋዩ የሚፈለግ የታክስ ዕዳ መጠን፣ የታክስ ዓይነት፣ የታክስ ዕዳው ያለበት ሁኔታ፣ የታክስ ከፋዩ የታክስ አከፋፈል ታሪክ በልዩ ሁኔታ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የጠየቀበት ምክንያት አጣርቶ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለክልሉ የግብር አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት ይልካል።

6/ የክልሉ የግብር አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሮ ለገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይም ለወከለው የሥራ ሃላፊ አቅርቦ በሚወሰነው መሰረት እንዲፈጸም ለመምሪያው ወይም ለጽ/ቤቱ መልሶ ያስተላልፋል።

7/ የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይም የወከለው የሥራ ሃላፊ የክፍያ ስምምነት ውል ለገባ ታክስ ከፋይ ያለበትን የእዳ ጫና ከግምት ውስጥ በማስገባት የቅድሚያ ክፍያውን እስከ 15 በመቶ ዝቅ ሊያደርግ ይችላል።

12. <u>የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ አቀራረብ ስለሚፈቅደው አካል እና የአፈፃፀም ሥርዓት</u>

1/ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ የታክስ ዕዳውን አጠቃሎ በአንዱ የመክፈል አቅም የሌለው መሆኑን ገልጾ ጥያቄውን ለመምሪያው ወይም ለጽ/ቤቱ የግብር አወሳሰን፣ አሰባሰብና ክትትል ዋና ሥራ ሂደት ሲያቀርብ እና ምክንያቱ ተቀባይነት ሲያገኝ በዚህ መመሪያ በተገለጸው ሁኔታ የሚስተናገድ ይሆናል።

2/ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ከሆነ የግብር አወሳሰን፣አሰባሰብና ክትትል ዋና ሥራ ሂደት አስተባባሪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ባለው መሰረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት ሊፈቀድ ይችላል።

3/ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት በድጋሜ የቀረበ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ከሆነ የመምሪያው ወይም የጽ/ቤቱ ኃላፊ የሚፈቅድ ይሆናል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3፣ በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአንቀጽ 11 መሠረት ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የታክስ ከፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ

በመምሪው ወይም በጽ/ቤቱ ለሥራው አግባብነት ያለው የታክስ ዕዳ ክትትል ባለሙያ ወይም ይህን እንዲከታተል ውክልና የተሰጠው ባለሙያ የስምምነት ውል በማዘጋጀት ለሥራ ሂደት አስተባባሪው አቅርቦ እንዲፈረም ያደርጋል።

5/ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል በ3 ኮፒ ተዘጋጅቶ ዋናው ኮፒ ከማህደር ጋር ይያያዛል፣ 2ኛው ኮፒ ለግብር ከፋዩ ይሰጣል፣ 3ኛው ኮፒ በግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የሥራ ሂደት ለዕዳ ክትትል ባለሙያ ወይም የሚመለከተው ባለሙያ ለቀጣይ ክትትል ሥራ የሚያዝ ይሆናል።

6/ በክፍያ ጊዜ ስምምነት ውሉ መሠረት ክፍያ የሚፈጸምበት ቀን በበዓላት ወይም በእረፍት ቀናት ላይ ከዋለ ክፍያው በቀጣዩ የስራ ቀን መፈጸም አለበት።

7/ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የጳጉሜ ወር የነሐሴ ወር አካል ሆኖ ይቆጠራል።

8/ በየደረጃው የሚገኙ የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የሥራ ሂደት አስተባባሪ የክፍያ ጊዜ ስምምነት የገቡ ታክስ ከፋዮች የክፍያ ስምምነት የተገባበትን የታክስ ዓይነት፣ የታክስ ዘመን፣ ዋና ታክስ ፣ መቀጫ እና ወለድ፣ በቅድሚያ የተከፈለ ገንዘብ መጠን፣ ስምምነት የተገባበት ቀን እና የመክፈያ ጊዜ ያካተተ ዝርዝር መረጃ ሪፖርት በየወሩ እያዘጋጀ ለገቢዎች ቢሮ ለግብር አወሳሰን፣አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት ይልካል።

13. <u>የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል ግዴታን አለመፈጸም</u>

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ በውሉ መሠረት በየወሩ ካልከፈለ ታክስ ከፋዩ ክፍያውን ካቆመበት ጊዜ አንስቶ ያልተከፈለዉን ቀሪ ዋና ታክስ ፣ ወለድና መቀጫ ተሰልቶ በሙሉ እንዲከፍል በገቢዎች ቢሮ የግብር አወሳሰን፣ አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት በታክስ ህጉ መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ያቋረጠው ክፍያ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠ አቋርጦት የነበረውን ታክስ በስምምነት ውል ጊዜ ውስጥ ያልከፈለውን ወራት አጠቃሎ እና የወጡ ወጪዎችን ጨምሮ የከፈለ ከሆነ የስምምነቱ ውሉ ወቅታዊ ተደርጎ ሳይሰረዝ እንዲቀጥል ይደረጋል።

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ስራ ላይ በነበረዉ መመሪያ ተቀባይነት አግኝቶ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ተፈቅዶ በስምምነት ውሉ መሠረት በመከፈል ላይ ያለ የታክስ ዕዳ በነበረው መመሪያ መሠረት ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል።

2/ የጡረታ መዋጮ ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወጪ መጋራት ክፍያ እና የካፒታል ንብረትን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም በዚህ መመሪያ ተፈጻሚ አይሆንም፣

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም የካፒታል ንብረትን በማስተላለፍ የተገኘን የጥቅም በሂሳብ መዝገብ ውስጥ ተካቶ የቀረበ መሆኑ ከተረጋገጠ የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ለማቅረብ አይከለከልም።

15. ስለተሻሩ መመሪያዎች

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረኑ ማናቸውም ሰርኩላሮችና አሰራሮች እንዲሁም የታክስ የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ አገቢ 08/2011 በዚህ መመሪያ ተሽረዋል።

16. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ጥር 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ነው።

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ የሚነሳ መብት ወይም ግዴታ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በአስተዳደር ተቋሙ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

ባህር ዳር

ክብረት ማህሙድ ሁሴን

ቢሮ ሃላፊ